**የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢብአግ)**

**Ethiopian National United Front (ENUF)**

# የኢብአግ ትግልና ዓላማ በትክክለኛው አቅጣጫ በጽናትና በቆራጥነት ይቀጥላል

## በኢትዮጵያ፣ አፍሪቃ፣ አውሮፓ፣ ካናዳ እና አሜሪካ የሚገኙ የኢብአግ አባሎች የወጣ መግለጫ

ግንቦት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር /ኢብአግ/ መስራች የነበሩት ሳይንቲስት እንጂነር ቅጣው እጅጉ ድርጅቱን ሲመሰርቱ ኢብአግ ግልጽ ዓላማና ግብ ነበረው። ሕዝብን ከማደራጀትም አልፎ የድርጅቱ ዓላማ በሥራ እየተተረጎመ በየአህጉሩ የሚደረጉት እንቅስቃሴዎችና ጥረቶች መስመር እየያዙ በመጡበት ወቅት ነበር መሪው በድንገት ከዚህ ዓለም የተለዩት።

የእንጂነር ቅጣው እጅጉ ድካምና ሩጫ ከወገኖቻቸው ጋር ሆነው አገራቸውንና ሕዝባቸውን ከወያኔ መዳፍ ነፃ ማውጣት እንጂ የሥልጣንና ዝና ፍለጋ አልነበረም። በየአገሩ ካሉ አባሎቻቸው ጋር እየተመካከሩ፣ እየጎበኙና እያበረታቱ የድርጅቱ እንቅስቃሴ በተጀመረባቸው አካባቢዎች እየተመላለሱ ብዙ ሥራዎችን ሲያከናውኑ እንደነበር ሁላችንም ሕያው ምስክሮች ነን።

በዓለም ዙሪያ ያለን የኢብአግ አባሎች ድርጅቱ ከአራት ዓመት በፊት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከመስራቹ መሪያችን ጋር ብዙ ተግባራዊ ሥራዎችን አካሂደናል። እንጅነር ቅጣው በድንገተኛ ሞት እስከተለዩን ድረስ አብረን ስንታገል ቆይተን ድርጅቱን ለማጠናከር በእቅድ ላይ እያለን መሪያችን በድንገት ቢለዩንም፣ የጀመሩትን ዓላማና ትግል ከግቡ ለማድረስ ተስፋ ሳንቆርጥ እየታገልን እንገኛለን።

እንዲሁም ለአብነት ያህል ለመጥቀስ፣ በአሁኑ ወቅት የኢብአግ ዋና ጸሓፊ የሆኑት ዶክተር በቀለ ሞላ ለድርጅቱ ያበረከቱትን አስተዋጽኦና ድካም ለመዘርዘር ይከብዳል። ከሳይንቲስት ቅጣው ጋር በቅርብ ወዳጅነትና ድርጅቱንም ለማጎልበት በአሜሪካ፣ ካናዳ እና አውሮፓ ከእንጅነር ቅጣር ጋር በመጓዝና በማማከር፣ በእውቀታቸውም፣ በጊዜና በገንዘባቸው ለአገራቸው ጉዳይ እየታገሉ እጅግ ብዙ አስተዋጽኦ አድርገዋል። አሁንም በማድረግ ላይ ናቸው። በአሁኑም ጊዜ ድርጅቱ ያለበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ለማስተካከል ብዙ መሞከራቸውን በርካታ አባላቶች ምስክር ነን።

እንደዚሁም የካናዳው ተወካይና የድርጅቱ ምክትል ሊቀመንበር አቶ መላኩ ሥዩም በካናዳ ያለውን ድርጅት አስተባብረው የመሰረቱ፣ ከድርጅቱ መስራችና መሪ ከእንጅነር ቅጣው ጋር በጣም ብዙ ሥራዎችን የሠሩ ታታሪ እና ቆራጥ ታጋይ መሆናቸውን በኩራት ልንናገር እንችላለን። ከእንጅነር ቅጣው እጅጉ ጋር በአፍሪቃ አገሮችና በሌሎችም አገሮች እየሄዱ ከፍተኛ ሥራ ያከናወኑ መሆናቸውን እና እስከአሁንም ድረስ በቅንነትና በቆራጥነት እየታገሉና እያታገሉ ይገኛሉ። እሳቸውም ድርጅቱን ለማጠናከርና ለማስተካከል መሞከራቸውን አባላት እናውቃለን።

በአጠቃለይ በኢትዮጵያ፣ በጎረቤት አገሮች፣ በአውሮፓ፣ ካናዳና አሜሪካ የሚገኙ አባላት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይና የሚዘነጋ መሆን የለበትም። እንጅነር ቅጣው ካረፉ በኋላ በጊዜያዊ የድርጅቱ ሊቀመንበርነት እንዲመሩ

P. O. Box 21387, Washington, DC 20013 • U.S.A.•
Tel. (202) 785-1618
www.enufforethiopia.org

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
(ኢብአግ)

Ethiopian National United Front
(ENUF)

የተሰየሙት ኮሎኔል አሥራት ቦጋለ ግን ከአባላት ፍላጎትና እምነት ውጭ፣ ድርጅቱን ወደ ስህተት እና ጥፋት አቅጣጫ እየሠሩ ይገኛሉ:: በተለይም፣ በቅርቡ የወጡት ድርጅታዊ መግለጫዎች አብዛኛዎቹ አባላት ውይይት አድርገው ሳይመክሩበት በመውጣታቸው፣ ድርጅቱን ከፍተኛ አዘቅትና ችግር ውስጥ እየከተተው ስለሚገኝ፣ በተደጋጋሚም በአባላቱና በድርጅቱ ምክትል ሊቀመንበር በአቶ መላኩ ሥዩም እና በዋና ጸሐፊው በዶክተር በቀለ ሞላ የሚሰነዘሩትን ሀሳቦችና እርማቶች ባለመቀበል፣ ከአባላቱ ፍላጎትና እምነት እንዲሁም እውቅና ውጭ ውሳኔ በማድረጋቸው፣ ከሌሎች ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር እንካስላንቲያ ውስጥ በመግባት፣ ቅራኔ በመፍጠርና ችግር በማብዛት፣ በተደጋጋሚ ስህተት በማድረግ፣ የድርጅቱን ፖሊሲ የሚቃረን ተግባር በማሳየታቸው፣ በአገር ቤት በቆራጥነት የሚፋለሙት አባላት ላይ የኮሎኔል አሥራት ቦጋለ የአመራር ጉድለት የሞራል ውድቀት ስላስከተለባቸውና፣ የዚህ ዓይነት አካሄድ ደግሞ አባላት የለፉበትንና መስዋዕትነት የከፈሉበትን ትግል መና ማስቀረት ስለሆነ፣ አንድ እርምጃ መውሰድ ስላለባቸው፣ አባላቱ ከተወያዩና ጉዳዩን ከመረመሩ በኋላ፣ ከዚህ የሚከተሉትን አቋማቸውን ይፋ ለማድረግ ወስነዋል::

፩ኛ. የጀመርነውን ትክክለኛ ትግል አቅጣጫ በማሳት፣ የተከፈለውን መስዋዕትነትና ልፋት ውጤት አልባ ማድረጉን ልንቀበለው የማንችለው ጉዳይ በመሆኑ፣ ከዛሬ ከግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ጀምሮ ኮሎኔል አሥራት ቦጋለ ከኢብአግ መሪነት የተገለሉ መሆኑ እንዲታወቅና ከእኛ ጋር ያላቸው ግንኙነት ሁሉ የተቋረጠ መሆኑን፤ በድርጅቱ ስምና በአባላቱ ስም ምንም ዓይነት መመሪያ፣ መግለጫ፣ ወይም ወክለው መቅረብ የማይችሉ መሆኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንገልጻለን::

፪ኛ. ዋነኛ ጠላታችን የወያኔ ዘረኛና አገር አጥፊ ቡድን መሆኑን በመገንዘብ ከሌሎች ጋር ያለውን ልዩነት በማቻቻል ፍልሚያችንና ትኩረታችን ወያኔን በማንኛውም መንገድ ማስወገድ ላይ መሆን እንዳለበት እንዲታወቅልን እናስገነዝባለን።

፫ኛ. ባለፈው ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. በዩትሬክት ከተማ፣ ኔዘርላንድስ የተፈጠረውን አዲስ ትብብር አስመልክቶ የወጣው መግለጫ ከድርጅቱ አባሎች ፍላጎትና እምነት ውጭ መሆኑ ታውቆ፣ ይህ በቅንጅት፣ በኦነግ፣ በኦጋዴን፣ በሲዳማ፣ በኢሕአግ ድርጅቶች መካከል የተመሠረተው ትብብር በመሰረቱ መልካም ጅምር፣ እርምጃና ትክክለኛ አቅጣጫ በመሆኑ ደስታችንና ድጋፋችንንም እንገልጻለን:: ይህም ሂደት ትብብሩ ውስጥ ለጊዜው ያልገቡ ግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና ዴሞክራሲ እንቆማለን የሚሉ ድርጅቶች ሁሉ ተካተው ትግሉን እንዲያጠናክሩ እናሳስባለን።

፬ኛ. የኢብአአግ አባላት ትግል የእንጅነር ቅጣውን ራዕይና የኢብአግን ዓላማ በመከተል ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበርና አንድነቱንም ለማጠናከር፣ የሀገሪቱንም ልዓላዊነት ለመጠበቅ ከቆሙ ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመተባበርና በአንድነት ለመሥራት ስለሆነ አባላቱ ይህንንም በተግባር ለመተርጎም ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጣለን::

፭ኛ. የድርጅታችንን የወደፊት አቅጣጫና የሚደረጉትን አብይ ለውጦች በቅርብ ቀን ለሕዝብ ይፋ የምናደርግ መሆኑን እናስታውቃለን::

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቸርነትና በልጆቿ የተባበረ ትግል ነፃ ትወጣለች::

P. O. Box 21387, Washington, DC 20013 • U.S.A.•
Tel. (202) 785-1618
www.enufforethiopia.org